የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት

HOUSE OF PEOPLES'REPRESENTATIVES OF THE FDRE

# የከተማ መሰረተ ልማትና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ 2014 ዕቅድ

ህዳር 2014 ዓ/ም

አዲስ አበባ

## ማውጫ

ክፍል አንድ:  ነባራዊ ሁኔታ ዳሰሳ ( SWOT Analysis ) .......... 4
የቋሚ ኮሚቴ አደረጃጀትን በተመለከተ .......... 4
1.3. መልካም አጋጣሚዎች እና ስጋቶች .......... 8
1.4. የምክር ቤቱ ራዕይ፣ ተልዕኮ ፣ እሴቶች እና የቋሚ ኮሚቴ ትኩረት መስኮች .......... 9
1.4.1. ራዕይ .......... 9
1.4.2. ተልዕኮ .......... 9
1.4.3. እሴቶች .......... 9
**1.4.4. የቋሚ ኮሚቴ ትኩረት መስኮች** .......... 10
ክፍል ሁለት: የ2014 ዕቅድ ዓላማ ዋና ግቦች እና ዝርዝር ተግባራት .......... 10
2.3. የሚሰሩ ዋና ዋና ግቦች እና ዝርዝር ተግባራት .......... 10
ክፍል ሶስት : የዕቅድ አፈፃፀም አቅጣጫዎች .......... 14
የክትትልና ቁጥጥር አግባብ .......... 14
ክፍል አራት :  በዕቅድ አፈጻጸም ወቅት ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችና መፍትሄዎቻቸው .......... 15
ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች .......... 15
ለስራው የሚያስፈልግ በጀት .......... 16

## ፲. መግቢያ

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የሕዝብ ተወካዩች ም/ቤት በህገ መንግስቱ አንቀፅ 55 እና በም/ቤት አሰራርና የአባላት ሥነ ምግባር ደንብ ቁጥር 6/2008 በህግ ተለይተው ከተሰጡት ዋና ዋና ተልዕኮዎች መካከል ህግ የማውጣት፣ አስፈፃሚ አካላትን የመከታተል፣ የመቆጣጠር፣ የፓርላማ ዲፕሎማሲ እና የህዝብ ውክልና ስራ መሆኑ ይታወቃል፡፡

ቋሚ ኮሚቴዎችም በተዋረድ በስልጣናቸዉ ስር ያሉትን ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶችን የሚመለከቱ ጉዳዮችን በዕቅድ በመመራት ለምክር ቤቱ ዕቅድ ስኬት በጎ አስተዋፅኦ ማድረግ እንዳለባቸዉ ይታመናል፡፡ ስለሆነም የምክር ቤቱን ተልዕኮ ለማስፈፀም ከሚጠቀሚባቸዉ አደረጃቶች መካከል አንዱ የቋሚ ኮሚቴ አደረጃጀት ነዉ፡፡ በመሆኑም በ2014 የፀደቀዉን የአስፈፃሚዎችን አደረጃጀት ጋር በሚጣጣም መልኩ እንዲሁም ኢትዮጵያ አሁን ከደረሰችበት የዕድገት ደረጃና ነባራዊ ሁኔታ ግንዛቤ ዉስጥ በማስገባት የቋሚ ኮሚቴዎችን ተግባርና ኃላፊነት ለመወሰን ተሻሽሎ የወጣው የቋሚ ኮሚቴው አደረጃጀትና አሰራር መመሪያ ቁጥር 02/2014 ዓ/ም ከተዋቀሩ 11 የቋሚ ኮሚቴ አደረጃጀት ውስጥ የከተማ መሰረተ ልማትና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አንዱ ነው፡፡

የከተማ መሰረተ ልማትና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢና ም/ሰብሳቢ ጭምር በጠቅላላው 13 አባላት ያሉት አደረጃጀት ነው፡፡

በመሆኑም ቋሚ ኮሚቴው የ5ኛው ዙር የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ቋሚ ኮሚቴ አባላት በ6 ዓመታት ቆይታ የነበሩ ጥንካሬዎችና ድክመቶች በዝርዝር በመፈተሽ የምክር ቤት 5 ዓመት ዕቅድ (2014 — 2018) እና የ2014 የም/ቤቱ ዕቅድ መነሻ ህግ ማውጣት፣ ክትትል ቁጥጥርና የህዝብ ውክልና ስራ በመስራት የህዝብ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ ያስችል ዘንድ የ2014 በጀት ዓመት የከተማ መሰረተ ልማት እና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ዕቅድ በሚከተለው መልክ ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡

## ክፍል አንድ:  ነባራዊ ሁኔታ ዳሰሳ ( SWOT Analysis )

### የቋሚ ኮሚቴ አደረጃጀትን በተመለከተ

የከተማ መሠረተ ልማትና የትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አደረጃጀት በአስፈጻሚዉ የመንግስት አካል ላይ የተደረገዉን የአደረጃጀት ለዉጥ ተከትሎ የቋሚ ኮሚቴዎች ቁጥርና አደረጃጀትንም ለመወሰን በወጣዉ የዉሳኔ ሃሳብ ቁጥር 2/2014 መሠረት ለዉጥ የተደረገ ሲሆን ቀደም ስል 10 የነበረዉ የቋሚ ኮሚቴዎች ቁጥር ወደ 11 ከፍ ሰል የእያንዳንዱ ቋሚ ኮሚተ አባላት ከ 9 እስከ 13 እዲሆን ተደርገዋል፡፡ በዚህ መሠረት የከተማ መሠረተ ልማት እና የትንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴም አንዱ በመሆን በስሩ ሁለት የሚንስቴር መስሪያ ቤቶችን ይዘዉ ሥራዉን እንዲጀምር ሆነዋል፡፡ በአጠቃላይ ቋሚ ኮሚቴዉ ሁለት ሚ/ር ቤቶችንና በየስራቸዉ ያሉትን ተጠሪ ተቋማትን የሚመለከቱ ተልዕኮዎችን እንዲሰራ ተደርገዋል፡፡

| ተ.ቁ | ሚኒስቴር መስሪያ ቤት | ተጠሪ ተቋማት | ምርመራ |
|---|---|---|---|
| 1. | የከተማ መሠረተ ልማት ሚኒስቴር | 1.1. የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለስልጣን<br>1.2. የኮንስትራክሽን ማኔጅመንት እንስቲትዩት<br>1.3. የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር | |
| 2. | የትራንስፖርትና ሎጅስትክ ሚኒስቴር | 2.1. የኢትዮጵያ ሲቪል አቪየሽን ባለስልጣን<br>2.2. የኢትዮጵያ ማሪታይም ባለስልጣን<br>2.3. የመድን ፈንድ አስተዳደር<br>2.4. የፐብሊክ ሰርቪስ ትራነስፖርት አገልግሎት | |

- 6ኛ ዙር ሀገር አቀፍ በተደረገው ሰላማዊና ዲሞክራሲያዊ ምርጫ አብላጫ ድምፅ በማግኘት መንግስት የመሰረተው ብልፅግና ፓርቲ ኢትዮጵያን የአፍሪካ የብልፅግና ተምሳሌት ለማድረግ የ10 እና 5 ዓመት ስትራቴጂ እቅድ እና የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ በማቀድ የመንግስት ፖሊሲ አስፈፃሚ ተቋማት አማካኝነት ለህዝብ የተገባውን ቃል ለመፈፀም ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡

  በመሆኑም የአስፈፃሚ ተቋማት በአዋጅ የተሰጠውን ስልጣንና ኃላፊነት በተገቢው መልክ እንዲወጡ ለማስቻል ህግ ማውጣት፣ ክትትል ቁጥጥር እና የህዝብ ውክልና ተግባራትን በብቃትና ጥራት በመወጣት የህዝብ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥና ምላሽ ሰጭ ም/ቤት በመገንባት ሂደት የከተማ መሰረተ ልማት እና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በአዲስ መልክ ተሻሽሎ የተደራጀ ሲሆን ለቀጣይ የህዝብ አደራ በብቃት ለመወጣት ያስችል ዘንድ በ5ኛ ዙር የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት የነበረው ዘርፉ ቋሚ ኮሚቴ ጥንካሬዎችና ድክመቶች በሚከተለው መልክ ቀርቧል፡፡

## 1.1. በጥንካሬ የታዩ ጉዳዮች

- የ5ኛው ዙር የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት በህገ መንግስት የተሰጠውን ስልጣንና ተግባራትን መነሻ በማድረግ የአስፈፃሚ ተቋማት ያቀረቡትን የተለያዩ ህግ ማዕቀፎችን፣ ፖሊሲዎችን እና ከተለያዩ ሀገራት ጋር የተደረጉ ስምምነቶችን አበረታች መሆኑ፣
- ክትትልና ቁጥጥር የሚደረጉ ተቋማት የታቀዱ ዋና ዋና ተግባራት አፈፃፀም በየጊዜ እየተሻሻለ መምጣቱ፣
- አስፈፃሚ ተቋማት ለም/ቤት ተልዕኮ አፈፃፀም እና የህዝብ ውክልና በተገቢው መንገድ ለመፈፀም የሚደረግ ጥረት እየተሻሻለ መምጣቱ፣
- በም/ቤት የሚሰሩ ተግባራትን ሙያዊ ደጋፍ የሚያደርጉ ባለሙያዎች መኖራቸው፣
- የየሩብ ዓመቱን ሪፖርት አላላክ በተመለከተ አብዛኛው መ/ቤት ቋሚ ኮሚቴው ባስቀመጠው የጊዜ ሠሌዳ መሰረት ወር በገባ እስከ አምስተኛው ቀን መላክ እየተለመደ መምጣቱ፣

- የመስክ ምልከታን በተመለከተ በየጊዜው በሚደረገው የድንገተኛ የመስክ ምልከታም ሆነ በመደበኛ የመስክ ምልከታ በማካሄድ ፕሮጀክቶች በተመደበላቸው በጀትና በተቀመጠላቸው ጊዜ ገደብ ውስጥ ተጠናቀው ለአገልግሎት እንዲውሉ ስለመደረጉ የማረጋገጥ ሥራ ሲሰራ መቆየቱ፣

- ቋሚ ኮሚቴዉ ከአብዛኛዉ ቋሚ ኮሚቴዎች ጋር የሚያገናኘዉ በመሆኑ የጎንዮሽ ግንኙነት የተሳለጠና ጠንካራ እንደ ነበረ መገንዘብ ይቻላል፡፡

- ትራንስፖርት ሚኒስቴር ላይ ለብዙ ዓመታት ሲንከባለል የነበረው ብሔራዊ የትራንስፖርት ዘርፍ ፖሊሲና ብሔራዊ የሎጀስቲክ ዘርፍ ፖሊሲ እንዲሁም የኢትዮጵያ ሞተር አልባ ትራንስፖርት ስትራቴጂ ተዘጋጅተው በሥራ ላይ እንዲውሉ መደረጉ፣

- አዳዲስ፣ ወጭ ቆጣቢ እና ውጤታማ ቴክኖሎጂዎችን ከማልማትና ከማስተላለፍ አኳያ ዩኒቨርሲቲዎችን፣ የፈጠራ ባለቤቶችንና ትልልቅ ኩባንያዎችን ለይቶ በጋራ የሚሰራ መሆኑ እና ቴክኖሎጂ ለማሸጋገር ጥረት መደረጉ፣ (**ለአብነት** የባቡር ቴክኖሎጂ)

- የትራንስፖርት አገልግሎቶች አስተማማኝና ደህንነታቸው የተጠበቀ መሆናቸዉን ለማረጋገጥ የሚያስችል የቁጥጥርና ክትትል ስልት መዘርጋቱና ተግባራዊ መሆኑ፤

- በሃገራችን ውስን የነበረውን የደረቅ ወደብ አገልግሎት በተፈጠረው አዲስ የለውጥ አመራር መልካም አጋጣሚ መሰረት በማስፋትና በተሻለ ሁኔታ በማደራጀት ጥሩ ሊባል የሚችል በወደብ አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ እና የእቃዎች የወደብ ላይ ቆይታን በማሳለጥ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ማነቃቃት የተቻለ ሲሆን ለእዚህ ስራም ይወጣ የነበረ በርካታ ሚሊዮን ብር ወጪ ማዳን መቻሉ በአብነት ሊጠቀስ የሚችል ስራ ሆኗል፡፡

- በኢትዮጵያ አየር መንገድ የሚጓጓዘውን የደንበኞች የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት አቅርቦትና የጭነት አገልግሎት አቅርቦት መጠን በማስፋፋት፣ ፍጥነት ያለው አገልግሎት በመስጠትና እንዲሁም በዚሁ የአገልግሎት ዘርፍ በርካታ ግቦች ተይዘው

  ተግባራዊ እንቅስቃሴ ሲደረግ የቆየ ሲሆን የተያዙ ግቦች አፈፃፀማቸው ውጤታማ ይሆን ዘንድም በቋሚ ኮሚቴው ያላሰለሰ ቁጥጥር እና ድጋፍ ሲደረግ ቆይቷል። በመሆኑም በዘርፉ በርካታ ውጤቶች የተገኙና የአገልግሎት አሰጣጡም በአለም አቀፍ ደረጃ በተሻለ ሁኔታ ላይ እንዲገኝ ማስቻሉ፣

- በተወሰኑ ከተሞች የመሬት ይዞታ ማህደሮች ከኦርቶ ፎቶ እና ከካዳስተር መሰረታዊ ካርታ ጋር የማስተሳሰር ስራ ደረጃውን ጠብቆ የተከናወነ መሆኑን በመስክ በማረጋገጥ በግብረ-መልስ የተደገፈ ክትትልና ድጋፍ መደረጉ፣

- በመንገድ ልማት ዘርፍ ባሳለፍነው የስትራቴጂክ ዕቅድ ዘመን የተያዙ ግቦችን በብቃት በቅልጥፍና ለመፈፀምና ዘርፉ በዘላቂነት የመፈፀም አቅምን ለመፍጠር የተጠናከረ የቁጥጥር የክትትልና የድጋፍ ስራዎች የተከናወኑ ሲሆን ይህም በመሆኑ በሃገር አቀፍ ደረጃ የመንገድ ሽፋን በከፍተኛ ደረጃ እንዲያድግ ከማስቻሉ ጋር ተያይዞ የተቀላጠፈ የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲኖርና በሃገር ደረጃ እንዲመጣ የሚፈለገውን ጠቅላላ እድገት በማምጣት ረገድ የራሱን አስተዋፅኦ እንዲያበረክት መደረጉ፣
- የሲቪል አቪዬሽን ባለስልጣን የአየር ናቪጌሽን ፋሲሊቲዎችን የማስፋፋትና የማሻሻል፣ የአቪዬሽን ደህንነትን የማረጋገጥ እንዲሁም የሃገሪቱን የአየር ክልል በብቃት የማስተዳደር ኃላፊነቱን ይወጣ ዘንድ በቋሚ ኮሚቴያችን በተለያየ መልክ የሚገለፁ የቁጥጥር የክትትልና የድጋፍ ስራውን ሲያከናውን ቆይቷል። ስለሆነም በባለስልጣን መ/ቤቱ የተጣሉ ግቦች በተያዘላቸው የአፈፃፀም ልክ ተግባራዊ የሆኑ ሲሆን በአሁኑ ሰዓት በአየር አገልግሎት ዘርፉ ለተገኘው ውጤታማ ስራ የራሱን አስተዋፅኦ ማበርከቱ፣
- የማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣንና የኢ.ባ.ት.ሎ.አ.ድ የባሕር ትራንስፖርት ዘርፉን በባለቤትነት ይዞ ቀልጣፋና ተወዳዳሪ የባሕር ትራንስፖርት አገልግሎት በመስጠት የደንበኞችን እርካታ ከማረጋገጥ እንዲሁም በአገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ የራሱን አሻራ ለማሳረፍ በርካታ ተግባራትን ሲያከናውን የቆየ መሆኑና በዚህ በኩልም ከቋሚ ኮሚቴው በተሰጠው የስልጣን ክልል ውስጥ ተገቢውን ድጋፍ ሲያደርግ በመቆየቱ በዘርፉ በርካታ ውጤቶች እንዲገኙ አስችሎታል። ስለሆነም በሃገራችን እየተመዘገበ ላለው የኢኮኖሚ እድገት የራሱን አስተዋፅኦ ማበርከቱ፣

## 1.2. በድክመት የታዩ ጉዳዮች

- አንዳንድ ዘርፎች ለህዝብ ተጠቃሚነት ከፍተኛ ሚና ያላቸውን አዋጆችን ፈጥኖ ተግባራዊ በማድረግ ለህዝብ ጥያቄ ፈጣን ምላሽ ከመስጠት አንፃር ጉድለት መኖሩን **ለአብነት** የመሬት ሊዝ ማሻሻያ አዋጅ፣
- በትራፊክ አደጋ ምክንያት እየደረሰ ያለውን የአካል ጉዳት እና ንብረት መውደም ለመቀነስ በአሽከርካሪ ማሰልጠኛ ተቋማት ብቃት ማረጋገጫ ሥርዓት ያለውን ጉድለት ማረም ይጠይቃል፣
- በቤት ልማት አቅርቦት ያለውን ማነቆ በመፈተሽ የዜጎችን የቤት ጥያቄ መመለስ ይጠይቃል፣

- በም/ቤት ጽ/ቤት በኩል የሙያዊ ድጋፍ የሚሰጡ ባለሙያዎች እጥረት መኖሩ፣
- አንዳንድ ተቋማት ከህዝብ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ፈጣን ምላሽ ያለመስጠት፣

## 1.3. መልካም አጋጣሚዎች እና ስጋቶች

### 1.3.1. መልካም አጋጣሚዎች

- የባለፉት 6 ዓመታት የቋሚ ኮሚቴ አፈጻጸም እና የ2013 በጀት ዓመት የተገመገመ ሰነድ መኖሩ
- 6ኛ ዙር የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት የሙያ፤ የልምድ፤ የማህበራዊ መሠረት ስብጥር በጣም አበረታች መሆኑ፣
- ባለፉት ዓመታት ያስመዘገብነዉ የዕድገት ደረጃችን የፋይናንስ አቅማችን ላይ መሻሻል እያሳየ መሆኑ፣
- የዓመቱ ዕቅድ ከአስር ዓመት ፍኖተ ብልፅግና የተቀዳና የአምስት ዓመት ስትራቴጅክ ዕቅድ መኖሩ፣
- በሀገሪቱ ላይ እየታየ ያለዉ የለዉጥ ጉዞ አበረታች መሆኑ እና በህዝብ የተመረጠ መንግስት ወደ ሥራ መግባቱ፣
- አሁን እየተፈጠረ ያለዉ ሀገራዊ ለዉጥና የህዝብ ተሳትፎ ማደግ የዓመቱን ዕቅድ ለማከናወን ተሰፋ ሰጭ መሆኑ፣

### 1.3.2. የሚጠበቁ ሥጋቶች

- በተለያዩ ምክንያቶች የቋሚ ኮሚቴ የተደራጀዉ ዘግይቶ መሆኑ የበጀት ዓመት ዕቅድ ግምገማም ሆነ የቁጥጥርና ክትትል ሥራችንን ጊዜ እጥረት ሊኖር ይችላል፣
- የተደራጀዉ ቋሚ ኮሚቴ በአጠቃላይ አዲስ መሆኑ በስራ ላይ የተወሰነ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያሳድር ይችላል፣
- ሀገራዊ የፀጥታ ሁኔታ በዚህ ከቀጠለ ቋሚ ኮሚቴ በተለያዩ ክልሎች ተንቀሳቅሶ እንዳይሰራ ማነቆ ሊሆን ይችላል፣

- ቋሚ ኮሚቴ የሚከታተላቸዉ ተቋማት በዕቅድ ዘመኑ በተቀመጠዉ የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ወቅታዊ ሪፖርት ያለመላክና በየሩብ ዓመቱ የግብረ መልስ ምላሽ ያለመስጠት ችግር ሊያጋጥም ይችላል፣

- ምክር ቤቱ በቋሚ ኮሚቴ ግብረ መልስ መሰረት ማስተካከያ ማድረግ በማይችሉ ተቋማት ላይ ተጠያቂነት በባለድርሻ አካላት በኩል የማስፈፀም ዉስንነት ሊገጥመዉ ይችላል፣

- በዓለም አቀፍና በሀገራችን እየተስፋፋ የመጣዉ የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ ለአጠቃላይ ሥራችን በተለይ ደግሞ ለቁጥጥርና ክትትል ሥራችን አደጋ ሆኖ ሊቀጥል ይችላል፣

## 1.4. የምክር ቤቱ ራዕይ፣ ተልዕኮ ፣ እሴቶች እና የቋሚ ኮሚቴ ትኩረት መስኮች

### 1.4.1.ራዕይ

ህገ-መንግስታዊ ኃላፊነትን የሚወጣ፣ የተለወጠ፣ ነፃ እና የህዝቦችን ፍላጐት የሚወክል ውጤታማና ምላሽ ሰጪ ምክር ቤት መሆን።

### 1.4.2.ተልዕኮ

የኢትዮጵያ ህዝቦችን ሰላም፣ ዴሞክራሲ፣ ልማት፣ አንድነት እና ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ የሚያስችል የውክልና፣ የህግ ማውጣት እና የክትትልና ቁጥጥር ህገ-መንግስታዊ ኃላፊነቱን በብቃት በመወጣት የህዝብ ድምፅ መሆን።

### 1.4.3. እሴቶች

- ሕገ መንግስታዊነት
- ብዝሃነት፣ ወንድማማችነት እና እህትማማችነት
- ለብሔራዊ ጥቅም ቅድሚያ መስጠት
- መከባበርና የጋራ መግባባት
- ታማኝነትና ቁርጠኝነት
- ተደራሽነት፣ ምላሽ ሰጪነት እና ተጠያቂነት
- ለአሬንጓዴ ልማት ተቆርቋሪነት

- ቀልጣፋና ወጪ ቆጣቢነትን ከፍ በማድረግ የምክር ቤቱን ራዕይ፣እሴትና ተልዕኮን የቋሚ ኮሚቴያችን የራሱ በማድረግ ለተግባራዊ ስኬት እንተጋለን፡፡

### 1.4.4.የቋሚ ኮሚቴ ትኩረት መስኮች

ትኩረት መስክ 1፦ ክትትልና ቁጥጥር

ትኩረት መስክ 2፦ ህግ ማውጣት

ትኩረት መስክ 3፦ የህዝብ ውክልና ስራዎች

## ክፍል ሁለት: የ2014 ዕቅዱ ዓላማ ዋና ግቦች እና ዝርዝር ተግባራት

### 2.1. የዕቅዱ ዋና ዓላማ

በአገራችን የተጀመረውን የለውጥ ጉዞ የሚያሳኩ የአሰራር እና የአደረጃጀት ማሻሻያዎችን በማድረግ፣ ሁለንተናዊና ተቋማዊ የአመራር ብቃት በማጎልበት በሕጉ የተሰጡትን ተግባራት በውጤታማነት ማከናወን በ6ኛ ብሔራዊ ምርጫ ለህዝብ የተገባውን ቃል ለመፈፀም ህግ ማውጣት፣ ክትትል ቁጥጥር እና የህዝብ ውክልና ተግባራትን በብቃትና ጥራት በመወጣት የህዝብ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥና ምላሽ ሰጭ ም/ቤት በመገንባት የህዝብ አደራ በብቃት ለመወጣት እንዲያስችል ነዉ፡፡

### 2.2. ዝርዝር ዓላማዎች

- ለቋሚ ኮሚቴ የሚቀርቡ ረቂቅ ሕጎች፣ ፖሊሲዎች እና እስትራቴጂዎች በግልፅነት፣ በተጠያቂነት አሰራር እና በታቀደ መንገድ በህዝብ ተሳትፎ እንዲወጡ ማድረግ፤
- የክትትልና ቁጥጥር ሥራዎች በአሰራር፣ በተደራጀ መረጃ፣ በህዝብ ተሳትፎ፣ በዲሞክራሲ ተቋማት ሪፖርቶች በመታገዝ የሕግ የበላይነት እንዲከበር፣ ተጠያቂነት እንዲሰፍን እና የዜጎች መብቶችና ጥቅሞች እንዲረጋገጡ ማድረግ፣

### 2.3. የሚሰሩ ዋና ዋና ግቦች እና ዝርዝር ተግባራት

**ግብ 1፦ ብቃት ያለው ዕቅድ ማዘጋጀትና መግባባት መፍጠር ተችሏል።**

**ዝርዝር ተግባራት**

1.1. 5ኛ ዙር ም/ቤት የዘርፍ ቋሚ ኮሚቴ ነባራዊ ሁኔታ ግምገማ መነሻ የ2014 ዓ.ም የቋሚ ኮሚቴ ዕቅድ ማዘጋጀት፣

1.2. የተዘጋጀውን ዕቅድ ለሁሉም ቋሚ ኮሚቴ አባላት በማቅረብ በግብዓትነት ማካተት ተችሏል፣

1.3. በቋሚ ኮሚቴ ደረጃ የፀደቀውን ዕቅድ ለም/ቤት አስተባባሪ ኮሚቴ ማቅረብ እና እንዲፀድቅ ማድረግ ተችሏል፣

**ግብ 2፦** የቋሚ ኮሚቴ አባላት የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠት ተችሏል።

**ዝርዝር ተግባራት**

2.1. የከተማ መሰረተ ልማትና ትራንስፖርት ቋሚ ኮሚቴ አባላት የስልጠና ፍላጐት መለየት እና በም/ቤቱ ጽ/ቤት አማካኝነት ስልጠና እንዲሰጥ ማድረግ፣

2.2. ቋሚ ኮሚቴ ክትትልና ቁጥጥር የሚያደርጋቸውን ሚኒስቴር መስሪያ ቤት እና ተጠሪ ተቋማት በሚሰሩ ተግባራት ግንዛቤ መድረክ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ማዘጋጀት።

2.3. ቋሚ ኮሚቴ ክትትልና ቁጥጥር የሚያደርጋቸውን ሚኒስቴር መስሪያ ቤት እና ተጠሪ ተቋማት ፖሊስ፣ ስትራቴጂክ ዕቅድ እና ዋናዋና ትኩርት መስኮች በዓመቱ መጀመሪያ ላይ የተደራጃ ስልጠና መስጠት

**ግብ 3፦** የክትትልና ቁጥጥር ተግባራትን በብቃት በመፈፀም የህዝብ እርካታ ማረጋገጥ ተችሏል።

**ዝርዝር ተግባራት**

3.1. በዓመት 3 ጊዜ የተቋማትን ሪፖርት በወቅቱ መቀበል እና ግብረ-መልስ መስጠት ተችሏል።

3.2. በዓመት 3 ጊዜ የአስፈፃሚ ተቋማትን መደበኛ ተግባራትን በቼክ-ሊስት የተደገፈ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ግብረ-መልስ መስጠት ተችሏል።

3.3. በዓመት 10 ጊዜ የመስክ/ፕሮጀክት ምልከታ በማድረግ ግብረ-መልስ መስጠት ተችሏል።

3.4. በዓመት 9 ጊዜ ድንገተኛ ምልከታ ማድረግ።

3.5. ከህዝብ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን/ጥቆማዎችን በመቀበል ተገቢነትን በማረጋገጥ 100% በህግ መሰረት የሚመለከታቸው አካላት ምላሽ እንዲሰጡ ማድረግ።

3.6. በዓመት 3 ጊዜ አስፈፃሚ አካላት ለም/ቤት በአካል ሪፖርት እንዲያቀርቡ ማድረግ ተችሏል።

**ግብ 4** ብቃትና ጥራት ያለውን የህግ ማዕቀፍ ፖሊሲዎችና አዋጆችን ማዘጋጅት ተችሏል ::

**ዝርዝር ተግባራት**

4.1 አስፈፃሚ ተቋማት ጥያቄ መሰረት አዳዲስ የህግ ማዕቀፎችን ማዘጋጀት ተችሏል

4.2 ህግ የማመንጨት ስልጣን ያላቸው አካላት (ተቋማት) የሚቀርቡ ጉዳዮችን በዝርዝር በመፈተሽ አዲስና ነባር አዋጆችን፤ ፖሊሲዎችን ማሻሻል ተችሏል::

**ግብ 5** የህዝብ ውክልና ስራ በተገቢው መልክ መፈፀም ተችሏል ::

**ዝርዝር ተግባራት**

5.1 አባላት በየምርጫ ጣቢያዎች በከተማ መሠረተ ልማት ትራንስፖርትና ሎጂስቲክ ዘርፍ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን በማደራጀትና አስፈላጊነትን በቋሚ ኮሚቴው ደረጃ በማረጋገጥ የሚመለከታቸው አካላት ምላሽ እንዲሰጡ ማድረግ፣

**ግብ 6** በቋሚ ኮሚቴው አማካኝነት የሚፈፀሙ ተግባራት ለህዝብ ግልፀኝነት ተፈጥሯል፡፡

**ዝርዝር ተግባራት**

6.1 በቋሚ ኮሚቴው አማካኝነት በህገ መንግስት የተሰጠውን የህዝብ ውክልና የዜጎችን ተሳትፎ እና ተጠቃሚነትን በሚያሰሉበት መልኩ የሚሰሩ ተግባራትን የሚዲያ ሽፋን እንዲያገኝ ማድረግ፣

6.2 የመስክ ምልከታ እና አፋፃፀም ግምገማ መረጃ የተለያዩ ሚዲያዎችን በመጠቀም ለህዝብ ተደራሽ ማድረግ፣

6.3 በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች የህዝብ ምክክር መድረክ በማዘጋጀት ግልፀኝነት መፍጠር ተችሏል፡፡

**ግብ 7. የተጠያቂነትን ሥርዓት መዘርጋት**

**ዝርዝር ተግባራት**

7.1 በየተቋማቱ በዕቅዱ ትኩረት መስኮችና በተገኙ ውጤቶች መሰረት የአስፈፃሚ ተቋማት ወጥ የሆነ መለኪያ በማዘጋጀት ምዘና ተደርጎ ደረጃ መለየት ተችሏል፡፡

7.2 የተሻለ አፈፃፀም ላመጡ ተቋማት የእውቅና መድረክ ማዘጋጀት፡፡

7፣3 ችግር ያለባቸውን ተቋማት በመለየት ተጠያቂነትን ማስፈን፡፡

**ግብ 8.** ቋሚ ኮሚቴው ክትትል በሚያደርግባቸው ዘርፎች ለህዝብ ጠቀሜታ ያላቸውን ጉዳዮችን በመለየት 2 ጥናትና ምርምር ስራዎችን መስራት ተችሏል፡፡

8.1 የጥናትና ምርምር ተግባራትን ማከናወን የሚችሉ ዩኒቨርስቲዎችን ከም/ቤት ጽ/ቤት ጋር በመቀናጀት መለየት ተችሏል፡፡

8.2 ለህዝብ ጥቅም ያላቸውን ዋና ዋና ጉዳዮች በመለየት ጥናት ማድረግና የሚመለከታቸው አካላት ተግባራዊ እንዲያደርጉ ክትትል ማድረግ ተችሏል፡፡

**ግብ 9.** የመልካም አስተዳደር ጉዳዮች እና ሌብነትን ትግል የሚደረግበት አካባቢ በተገቢው ትኩረት መሰጠቱ ተረጋግጧል፡፡

9.1 በሁሉም ሴክተር መስሪያ ቤቶች የመልካም አስተዳደር እና ሌብነትን ትግል ማድረግ በሚያስችል መልክ በዕቅድ የተካተተ መሆኑን ማረጋገጥ፣

9.2 መልካም አስተዳደር እና ሌብነት በሚመለከት በየሩብ ዓመት የእቅድ ክንውን ሪፖርት አካል መደረጉን ማረጋገጥ፣

9.3 በየሴክተር መስሪያ ቤቶች ዜጎች ያገኙትን ተጨባጭ ውጤት ማዕከል ያደረገ የተገልጋዮች እርካታ መረጋገጡን ማረጋጋጥ፣

**ግብ 10.** የሴክተር ክልል ( cross cutting issuer) ተግባራት በተገቢ መልክ ታቅዶ እየተፈፀሙ መሆናቸውን መከታተል ተችሏል፡፡

**ዝርዝር ተግባራት**

10.1 የሴቶች ወጣቶች ህፃናት ከኤች አይቪ ኤድስ ጋር ያሉ ዜጎች አካል ጉዳተኞች ተሳትፎ እና ተጠቃሚነትን በሚመለከት ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፡፡

10.2 ሁሉም የመንግስት አስፈፃሚ ተቋማት አካባቢ ጥበቃ ሥራዎችን አሰተዋፅኦ እያደረጉ መሆናቸውን መከታተል፡፡

**ግብ 11.አዳድስ የተክኖሎጅ አጠቃቀምና ምርጥ ተሞክሮችን ተግባራዊ እየተደረጉ መሆኑ**

**ዝርዝር ተግባራት**

11.1 አዳድስ ቴክኖሎጅችን በመጠቀም የሜጋ ፕሮጀክቶችን የግንባታ ሂደትና ጥራት በተሟላ መለኩ ክትትልና ቁጥጥር መደረጉን መከታተል

11.2 ምርጥ ተሞክሮችን በመቀመር የተሸለ ዉተት እንደመጣ ጥረት መደረጉን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ

## ክፍል ሶስት ፡ የዕቅድ አፈፃፀም አቅጣጫዎች

- ሁሉንም ዕቅዶች በተቀመጠላቸው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ሳይንጠባጠቡ እንዲፈፀሙ በቼክ ሊስት የምንመራ ይሆናል፣
- ወቅታዊ ሁኔታዎችን በማየት እንደአስፈላጊነቱ ዕቅዳችንን በመከለስ መካተት የሚገባቸውን በማካተትና ላይሰሩ የሚችሉ በዕቅዱ ውስጥ ያሉ ጉዳዮችን የማውጣት አቅጣጫን እንከተላለን፣
- ከምንከታተላቸዉ ተቋማት ዉስጥ የተለየ ትኩረት የሚሹትን በመለየት አተኩረን እንሰራለን፡፡
- ከስራችን ጋር ግንኙነት ካላቸውና ከባለድርሻዎቻችን ጋር በመቀናጀትና በመናበብ ተግባራትን የመፈፀምና የማሳካት አቅጣጫ ይኖረናል፣
- ለመስክ ምልከታ ስራዎቻችን የሰው ሀይሉን በመደልደል በበቂ ዝግጅት ላይ የተመሰረተ እንዲሆን እናደርጋለን፣
- ለህዝብ ተሳትፎ መድረኮች ልዩ ትኩረት በመስጠት የመፈጸም አቅጣጫን የምንከተል ይሆናል፡፡

### የክትትልና ቁጥጥር አግባብ

- ቼክ-ሊስቱን መሰረት በማድረግ አጫጭር የሥራ ላይ ግምገማዎችን በማድረግ የሚንጠባጠቡ ተግባራት እንዳይኖሩ ጥረት ማድረግ፣

- በቋሚ ኮሚቴ ደረጃ በየወሩ የተግባራት አፈፃፀም ግምገማ ማድረግና የየወሩን አፈፃፀም ሪፖርት ለሚመለከታቸው አካላት መላክ፣
- በዓመት ሁለት ጊዜ (ጥርና ሰኔ) ዝርዝር ግምገማ በማድረግ የተግባራት አፈፃፀም ያለበትን ደረጃ በማስቀመጥ ለቀጣይ መዳበር የሚገባቸውንና መስተካከል የሚገባቸውን እየለየን ለተሻለ ውጤት መረባረብ፣

## ክፍል አራት ፡ በዕቅድ አፈጻጸም ወቅት ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችና መፍትሄዎቻቸው

**ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች**

- አስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶች ዕቅድና ሪፖርታቸውን በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ የማቅረብ ውስንነት ሊኖር ይችላል፣
- የመስክ ምልከታ ለማካሄድ የበጀት፣ የተሽከርካሪና የጊዜ እጥረት እንዲሁም በቂ የሚዲያ ሽፋን ያለማግኘት ችግር ሊያጋጥም ይችላል፣
- ለኮሚቴው ለስራ ምቹ ሁኔታን ከመፍጠር አንጻር በም/ቤቱ ጽ/ቤት በኩል ለስራ አስፈላጊ የሆኑ ግብአቶችን በወቅቱ የማቅረብ ውስንነት ሊያጋጥም ይችላል፣
- የቋሚ ኮሚቴው የስራ ቀናት በም/ቤቱ የመወሰድ ሁኔታ ሊከሰት ይችላል፣
- ለስራችን ስኬታማነት የጊዜ ዕጥረት ትልቁ ማነቆአችን ሊሆን ይችላል፡፡

### ለሚያጋጥሙችግሮች የተቀማጡየ መፍትሄ እርምጃዎች

- አስፈፃሚ መ/ቤቶች ዕቅድና የአፈጻጸም ሪፖርታቸውን በወቅቱ እንዲያቀርቡ ማሳሰብና በኮሚቴው ቼክ ሊስት ላይ አስቀድሞ መግባባት፣
- የመስክ ምልከታ ፕሮግራምን አስቀድሞ ለጽ/ቤቱ ማቅረብና ማሳወቅ፣
- አስፈላጊ የግብአት ጥያቄዎችን አስቀድሞ በማሳወቅ ችግሩን ማቃለል፣ የቢሮና አዳራሽ ችግሮች እንዲፈቱ ከጽ/ቤቱ ጋር መናበብ፣
- በመናበብና በጋራ መግባባት ያለውን ጊዜ አጣጥሞ በመጠቀም ተግባራትን ማሳካት፣

## ለስራው የሚያስፈልግ በጀት

### የከተማ መሠረተ ልማት እና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በ2014 በጀት ዓመት ጠቅላላ በጀት

| ተ.ቁ. | የበጀት ርዕስ | የበጀት ፍላጐት |
|---|---|---|
| 1 | **የመስክ ምልከታ** | |
| 2 | መደበኛ መስክ | 2,087,962.78 |
| 3 | የከተማ መስክ | 107,983.70 |
| 4 | ድንገተኛ መስክ | 125,859.71 |
| 5 | የቅንጅት መስክ | 154,303.05 |
| 6 | የምክክር መድረክ | 346,300.00 |
| 7 | የመስተንግዶ ወጪ | 136,000.00 |
| 8 | የመጽሄት ማሳተሚያ | 400,000.00 |
| **9** | **ጠቅላላ ድምር** | **3,358,409.24** |

# ተግባራት የሚፈፀሙበት የጊዜ ሰሌዳ

| ተ/ቁ | ዝርዝር ተግባራት | ህዳር | ታህሳስ | ጥር | የካቲት | መጋቢት | ሚያዝያ | ግንቦት | ሰኔ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ➢ የቋሚ ኮሚቴ ዕቅድ ማዘጋጀትና ከሁሉም አባላት ጋር መግባባት በመፈጠሩ ለም/ቤት ጽ/ቤት ገቢ ማድረግ፣ | ✓ | | | | | | | |
| 2 | ➢ የቋሚ ኮሚቴ የጊዜ ሰሌዳ የያዘ ቼክ ሊስት ማዘጋጀትና የጋራ መግባባት መፍጠር፣ | | ✓ | | | | | | |
| 3 | ➢ የቋሚ ኮሚቴ አባላት የስልጠና ፍላጎት በመጠየቅ በም/ቤት ጽ/ቤት አማካኝነት ስልጠና እንዲሰጥ ማድረግ፣ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | | | | |
| 4 | ➢ የቋሚ ኮሚቴ ክትትልና ቁጥጥር የሚያደርግባቸው ሚኒስቴር መስሪያ ቤት እና ተጠሪ ተቋማት፣ ፖሊሲዎች ስትራቴጂክ ዕቅድ እና የትኩረት መስኮች ስልጠና መስጠት፣ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | | | | |

| ተ/ቁ | ዝርዝር ተግባራት | ህዳር | ታህሳስ | ጥር | የካቲት | መጋቢት | ሚያዝያ | ግንቦት | ሰኔ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 5 | ➢ የተቋሙን ዕቅድ ሪፖርት በወቅቱ መቀበልና ግብረ መልስ መስጠት፣ | | ✓ | | | ✓ | | | ✓ |
| 6 | ➢ የተቋሙን ተግባራት በቼክ ሊስት የተደገፈ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ እና ግብረ መልስ መስጠት፣ | | ✓ | | | ✓ | | | ✓ |
| 7 | ➢ የመስክ ፕሮጀክት ምልከታ በማድረግ ግብረ መልስ መስጠት፣ | | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |
| 8 | ➢ ከህዝብ የሚቀርቡ ቅሬታዎች፣ ጥቆማዎች በመቀበል ተገቢነትን በማረጋገጥ 100 % ምላሽ እንዲያገኝ ማድረግ፣ | | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |
| 9 | ➢ የቋሚ ኮሚቴው የወር፣ የሩብ፣የግማሽ ዓመት፣ እና ሩብ ዓመት እና የዓመት ማጠቃለያ ሪፖርት ማዘጋጀት እና ለም/ቤት (ለሚመለከተው ) አካል መላክ፣ | | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | | |
| 10 | ➢ የተለያዩ የህግ ማዕቀፎችን፣ ፖሊሲዎችን፣ማዘጋጀት እና በም/ቤቱ እንዲፀድቅ ማድረግ፣ | | | ✓ | | | | | ✓ |
| 11 | ➢ የመስክ ምልከታ የህዝብ ውይይት ስልጠናና የአፈፃፃም ግምገማ፣ የሚዲያ ሽፋን እንዲያገኝ በማድረግ ለህዝብ ግልፀኝነት መፍጠር፡፡ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |
| 12 | ➢ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች እና ተጠሪ ተቋማት በዕቅድ ክንውን አፈፃፃም እና በተገኙ ውጤቶች መሰረት ወጥ ቼክ ሊስት በማዘጋጀት ጥረት ማድረግ፡፡ | | | | | | | | ✓ |
| 13 | ➢ የተሻለ ውጤት ያመጡ ተቋማትን ማበረታታትና ችግር ያለባቸውን ተቋማትን በመለየት ተጠያቂነትን ማስፈን፡፡ | | | | | | | | ✓ |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 14 | ➢ ለህዝብ ጠቀሜታ ያላቸውን ርዕሰ ጉዳዮችን በመለየት 2 ጥናትና ምርምር ተግባራት ከም/ቤቱ ጽ/ቤት ጋር በመቀናጀት ከዩኒቨርስቲዎች ጋር በትስስር ማጥናት፣ | | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |
| 15 | ➢ የጥናቱን ግኝት የሚመለከታቸው የመንግስት ተቋማት ተፈፃሚ መሆኑን ክትትል ማድረግ፣ | | | | | | | | ✓ |
| 16 | ➢ ክትትል በሚደረጉ ሴክተር ተቋማት ሌብነትና መልካም አስተዳደር ችግሮችን ስልት በመቀየስ ውጤት እያመጡ መሆናቸውን መከታተል፣ | | | ✓ | | | | | ✓ |